# የአ/ከ/አስ/ር ወረዳ ሁለት ንግድ ኢንዱስትሪ ትራንስፖርት ጽ/ቤት ከ2015(1/2) እስከ 2017 ዓ.ም የተከለሰ ስትራቴጂክ የልማት ዕቅድ

ኅዳር 22/2016 ዓ.ም
አሶሳ፤

**መግቢያ፡-**

የአሶሳ ከተማ አስተዳደር ወረዳ ሁለት ንግድ ኢንድስትሪ ትራንስፖርት ጽ/ቤት መንግስት ባለፈዉ ስትራቴጂክ ዘመን ያሉበትን ሰፊ የልማትና የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመቅረፍ ተከታታይ የሆነ ጥረት ማድረጉና አበረታች ዉጤቶችን ማስመዝገቡ ይታወቃል፡ ለውጤቶቹ መገኘት ከፍተኛዉን አስተዋጽኦ ያደረጉት ባለፉት አምስት ተከታታይ ዓመታት ዉጤታማነታቸውን በተግባር ያረጋገጡት ሀገራዊ የልማትና የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ሲሆኑ በሃገር አቀፍ ደረጃ የተያዘው የረዥም ዘመን ጠቋሚ የልማት እቅድ ላይ በመመርኮዝና ትኩረት የተሰጠባቸውን አቅጣጫዎች በመከተል በከተማችን ተፈፃሚ ለማድረግ የተደረገ ጥረት እና ከክልል ንግድ የሚወርድልንለይተን ስትራተጂያዊ ዕቅድ በማዘጋጀት ሰፊ እንቅስቃሴ በማድረጋችን የከተማውን መልካም አስተዳደር ችግሮች ለማስፈን ፤ሰላም እንዲሰፍንና የህዝቦች ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ በየደረጃዉ ያለዉ መዋቅራችን ርብርብ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡በዚሁ መሰረት የለውጥ መሳሪያዎችን ተግባራዊ በማድረግ ጥራት ያለውና ፈጣን አገልግሎት በማረጋገጥ ደንበኞችን በማርካት ቀጣይነቱን ለማረጋገጥ የተለያዩ ተግባራት በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡ የተጀመረውንም የለውጥ ሂደት ቀጣይነቱን ለማረጋገጥ እንዲቻል የዘመኑ ቴክኖሎጂ ባፈራው ስትራቴጂያዊ የስራ አፈፃፀም አመራርና ምዘና ስርዓት መጠቀም የግድ የሚል በመሆኑ ስትራቴጂያዊ የስራ አመራርና ውጤት ተኮር ምዘና ስርዓት ጥናት ማካሄድና ወደ ተግባር መሸጋገር አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ይህን እድገት ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግ ሀገራዊ የዕድገትና የትንራስፎርሜሽን ዕቅድ ተዘጋጅቶ ሰፊ እንቅስቃሴ እየተደረገ ሲሆን መምሪያችን የመንግስትን የልማት እቅድና የትኩረት አቅጣጫ ባገናዘበ መልኩ በአዲሱ የዉጤት ተኮር ስርዓት የተቃኘ ሊተገበር የሚችል የቀጣይ 2015(1/2) እስከ 2017 ዓ.ም የተከለሰ ስትራቴጂክ፤የልማት፣ዕቅድለማዘጋጀትተችሏል፡፡

**የምራፍ-አንድ**

**1.ራዕይ፣ተልዕኮ ፣ ዓላማ ፣ ግብና እሴቶች፤**

**1.1.ራዕይ /VISSION/**

የንግድ ኢንዱስትሪ ትራንስፖርት የልማት ዘርፎች አድገውና በልጽገው ለህዝብ ምቹ በመሆን ህዝቡ ከድህነት እና ከስራ አጥነት ተላቆ አምራች ዜጋ ሆኖ ማየት፡፡

**1.2.ተልዕኮ /MISSION/**

ለንግዱ ማህረሰብና ለከተማው ነዋሪ አመቺ አከባቢያዊ ሁኔታን በመፍጠር ግልጽና ቀልጣፋ አገልግሎትና ድጋፍ በመስጠት ንግድ ትራንስፖርት ኢንዱስትሪ የልማት ዘርፎች እንዲስፋፉና እንዲጎልብቱ በማድረግ በከተማችን ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ኦኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት እንዲመጣ ማድረግ፡፡

**1.3./ዕሴቶች/VALUES/**

- ✓ ለደንበኞች እርካታ ቅድሚያ ትኩረት እንሰጣለን፣
- ✓ ግልፀኝነትና ተጠያቂነት ያለው አሰራር እናሰፍናለን፣
- ✓ ጠንካራ የስራ ተነሳሽነት እናዳብራለን፣
- ✓ ለሴክተሩ ልማትና እድገት በቁርጠኝነት እንቆማለን፣
- ✓ ደንበኞችን ያለአድሎ፣በታማኝነት፣በቅንነት፣በቅልጥፍናና በጥራት እናገለግላለን
- ✓ ኃላፊነትን እንወጣለን
- ✓ ተቀናጅቶ በቡድን የመስራት ባህል ማዳበር
- ✓ የስራ ነፃነት፣ተነሳሽነትና በራስ የመተማመን ባህል ማዳበር
- ✓ አሳታፊ አሰራር፣ግልጸኝነትና ባለሙያ የመጠቀም ባህል ማዳበር
- ✓ አዳዲስ እውቀቶችን የመሻት፣የመማርና የመለወጥ ባህል፣ማዳበር
- ✓ ቁጥጥር ደንብና መመሪያ ለውጤትና ለስኬት ማድረግ
- ✓ ለመንግስት ሀብትና ንብረት አጠቃቀምና ጥበቃ ተምሳሌት መሆን
- ✓ ስራአተ ፆታን ያገናዘበና በስነምግባር የታነፀ ሠራተኛን መፍጠር

1.4.የአሶሳ ከተማ አስተዳደር ወረዳ ሁለት ን/ኢ/ት  ሥልጣንና ተግባራት፡-

1) ንግድ፣ እንዲስፋፋ የተመቻቹ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ያደርጋል፤

2) በከተማችን ንግድን ለማስፋፋትና ለማጠናከር ቀልጣፋ የግብይት ሥርዓትና ተገቢ የንግድ አሠራር እንዲሰፍን ያደርጋል፤

3) አግባብ ባለዉ ሕግ መሠረት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት ይሰጣል፣ ፣ ይሰርዛል፣ የንግድ መዝገብ ያደራጃል፤

4) ተገቢ ያልሆኑ የንግድ አሠራር ለመከላከል የሚያስችል የተሟላ ሥርዓት ይዘረጋል፤የንግድ ህጎች መከበራቸዉን ያረጋግጣል፣ አፈፃፀማቸዉን ይከታተላል፤

5) በህጉ መሠረት ለሸማቾች ጥበቃ ያደርጋል፣ የንግድ ዕቃዎችንና ሥርጭት ይቆጣጠራል፤

6) በከተማችን የዋጋ ተመን ላይ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤

7) የከተማችን ህጋዊ ሥነ-ልክ ሥርዓት በአግባቡ መተግበሩን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል

8) በከተማችን የትራንስፖርት ህጎች እንዲከበሩ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል

9) በከተማችን የታሪፍና የፌርማታ ቁጥጥርና ክትትል ያደርጋል

10)የመንገድ ትራንስፖርት ህጎች መከበራቸዉን ይከታተላል፣ እርምጃ ይወስዳል፤

11)አሽከርካሪ ተሽከርካሪዎችን ይቆጣጠራል አስፈላጊውን እርምጃ ይወሰዳል

12)ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች እንዲስፋፉ ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር ድጋፍና ክትትል ያደርጋል

13)ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር የመንገድ ትራፊክ አደጋ ለመከላከል በቅንጅት ይሰራል፣ በከተማችን የመንገድ ትራንስፖርት እንዲሳለጥ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል

14)ዓላማዉን ለማስፈፀም የሚችሉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናዉናል፡

# ክፍል-ሁለት፤

## ለዕቅዱ ዝግጅት የተወሰዱ መነሻ ነባራዊ ሁኔታዎች ትንተና፣

### ከ2013 ዓ.ም እሰከ 2015(1/2)የተከለሰ የልማት እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ፡፡

**በንግድ ምዝገባ ፈቃድ ህጋዊ አሠራር ማስፈንና ማስፋፋት የተሠሩ ሥራዎች፤**

- ስትራቴጂክ የተከለሰ የልማት ዕቅድ አፈጻጸም (2013-2015(1/2) ዓ.ም)በአሶሳ በከተማችን ያሉ የንግድ ድርጅቶች ህጋዊነታቸዉን ለማረጋገጥ 14,273 ጠንካራ ክትትልና ቁጥጥር ስራ ለመስራት ታቅዶ 13,089 ንግድ ድርጅቶች ላይ የተሠራ ሲሆን አፈጻጸሙም 91.7% ማከናወን ተችሏል፡፡
- የመለኪያ መሠሪያዎችን ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ 1088 የጠረጴዛ ሚዛን፣ 610 የምድር ሚዛን፣ 336 የስጋ ሚዛን እና 132 ዲጅታል የወርቅ ሚዛን ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ታቅዶ 1003(92%) የጠረጴዛ ሚዛን፣ 751(92.7%) የምድር ሚዛን፣ 323(96%) የስጋ ሚዛን፣ 127(96%) ዲጅታል የወርቅ ሚዛን ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ አዲስ ንግድ ስራ ፍቃድ ለመስጠት 14076 ታቅዶ ለ 8884 ነጋዴዎች የንግድ ፈቃድ የተሰጠ ሲሆን አፈጻጸሙ በፐርሰንት ሲሰላ 63.1% ነው፡፡
- አዲስ የምዝገባ ፍቃድ ለመስጠት 5852 ታቅዶ ለ4298 ነጋዴዎች የንግድ ፈቃድ መስጠት የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ በፐርሰንት ሲሰላ 73.4% ተከናውኗል፡፡
- የንግድ ስራ ፍቃድ እድሳት 13,500 ታቅዶ 10092 የታደሰ ሲሆን በፐርሰንት ሲሰላ 74.7% ተከናውኗል፡፡
- የንግድ ምዝገባ እና የስራ ፍቃድ ማሻሻያ ለማድረግ 470 ታቅዶ 891 የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙ በፐርሰንት ሲለካ ›100 % ተከናውኗል፡፡
- ምትክ ምዝገባና የስራ ፍቃድ ለመስጠት 585 ታቅዶ 543 ተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙ ሲለካ 92.8% ተከናውኗል ፡፡
- ከአዲስ የንግድ ስራ ፍቃድ፤ ከፍቃድ እድሳትና ከተለያዩ ቅጣት ገቢ በብር **13,048,608** ለመሰብሰብ ታቅዶ **8,562,888** የተሰራ ሲሆን በፐርሰንት ሲሰላ **65.6%** ተከናውኗል፡፡
- ስኳር ለአራቱም ቀበሌ ሸማቾች፣ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ቡልቃትና አጉቤላ፣ የመንግስት ሠራተኞች ሸ/ህ/ስራማህበር 25,980 ኩንታል ታቅዶ 9881 የኩንታል ተሰራጨ ሲሆን አፈጻጸሙ በፐርሰንት ሲሰላ 38% ተከናውኗል፡፡
- እንዲሁም 14,233,740 የምግብ ዘይት ለመሠራጨት ታቅዶ 707,465 ሊትር የተሠራጨ ሲሆን፤ አፈጻጸሙ በፐርሰንት ሲሰላ 5% ተከናውኗል፡፡

**የግብርና ምርቶች ግብይት ዘርፍ ስትራቴጂክ የተከለሰ የልማት ዕቅድ አፈጻጸም (2013-2015(1/2) ዓ.ም)**

- አስገዳጅ የግብርና ምርቶች ለመጀመሪያ የግብይት ማዕከላት የቁም እንስሳት 163,438 ለማቅረብ ታቅዶ 138,496 የቀረበ ሲሆን አፈፃፀሙም 84.7% ተከናውኗል፡፡
- አስገዳጅ የግብርና ምርቶች ለመጀመሪያ የግብይት ማዕከላት ቆዳና ሌጦ 76,083 ለማቅረብ ታቅዶ 56,350 የቀረበ ሲሆን አፈፃፀሙም 74% ተከናውኗል፡፡
- አስገዳጅ የግብርና ምርቶች ከመጀመሪያ የግብይት ማዕከላት ወደ ማዕከላዊ ገበያ የተሸገ የቆዳና ሌጦ ምርት 57,332 ለማቅረብ ታቅዶ 32,797 የቀረበ ሲሆን አፈፃፀሙም 57.2% ተከናውኗል፡፡

<u>በእንዱስትሪ የስራ ዘርፍ ስትራቴጂክ የተከለሰ የልማት ዕቅድ አፈጻጸም (2013-2015(1/2) ዓ.ም)</u>

- የአምራች ኢንዱስትሪዎችን በማስፋፋት አቅም ለማሳደግ 61 ታቅዶ 53 የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙ 86.8% ተከናውኗል፡፡
- ለአምራች እንዱስትሪዎች ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ 750 ታቅዶ 680 የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙ 90.6% ተከናውኗል፡፡
- የአምራች ኢንዱስትሪዎችን በማስፋፋት 2015 የስራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ 1590 የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙ 78.5% ተከናውኗል፡፡
- የእንዱስትሪ ልማት ለማሳደግ የእንዱስትሪ ፓርክ 461 ለመከለል ታቅዶ 361 የተካለለ ሲሆን አፈጻጸሙ 78.3% ተከናውኗል፡፡

**በመንገድ ደህንነት ቡድን ዘርፍ የስትራቴጂክ የተከለሰ የልማት ዕቅድ አፈጻጸም** (2013-2015(1/2) ዓ.ም)

- በአሶሳ በከተማችን የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም በመንገድ ትራፊክ ደህንነት ዙሪያ ለህብረተሰብ ግንዛቤ ለመፍጠር 231,174 ታቅዶ 185,864 የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙ በፐርሰንት ሲሰላ 80.4% ተከናውኗል፡፡
- የህብረተሰቡን የመንገድ አጠቃቀም ግንዛቤ ለማሳደግ በትምህርት ቤቶች 36 የተማሪ ትራፊክ ክበባት ለማቋቋም ታቅዶ 38 የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙ በፐርሰት ሲሰላ ›100% ተከናውኗል፡፡እንዲሁም 36 የቀበሌ የመንገድ ደህንነት ም/ቤቶችን ለማቋቋም ታቅዶ 36 የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙ በፐርሰት ሲሰላ 100% ተከናውኗል፡፡
- የታችኛውን መዋቅር ድጋፍና ክትትል ለማድረግ 30 ታቅዶ 28 ጊዜ የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙ በፐርሰት ሲሰላ 93.3% ተከናውኗል፡፡

- ◈ የህዝብ ንቅናቄ በመፍጠር የህብረተሰቡን የመንግድ አጠቃቀም ግንዛቤ ማሳደግ 183,638 ታቅዶ 163,408 የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙ በፐርሰት ሲሰላ 89 % ነው::
- ◈ በትራንስፖርት ደንብ ጥሰት የተያዙ ተሽከርካሪዎች በሪከርድ እንዲመዘገቡ ለማድረግ 13,843 ታቅዶ 11,671 የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙ በፐርሰት ሲሰላ 84 % ነው:

## ➢ የትራንስፖርት ስምሪት አገልግሎት ስትራቴጂክ የተከለሰ የልማት ዕቅድ አፈጻጸም (2013-2015(1/2) ዓ.ም)

- ነባር መስመሮች እንዲሸፈኑ ለማድረግ 1338 ታቅዶ 1177 የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀሙ በፐርሰት 88% ነው፣
- በከተማ ታክሲ በምልልስ ተጠቅመው የተጓዘው ህዝብ ብዛት 856,156 ታቅዶ 741,463 የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀሙ በፐርሰት 86.4% ነው፣
- በመናኻሪያ ስምሪት በምልልስ ህዝብ ለማጓጓዝ 1,113,500 ለመስጠት ታቅዶ 958,783 የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀሙ በፐርሰት 86% ነው፣
- በህዝብ ማመላለሺያ ተሽከርካሪዎች ላይ ክትትልና ቁጥጥር ስራ ለማከናወን 908 ታቅዶ 818 የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀሙ በፐርሰት 90% ተከናውኗል፣
- ለተሽከርካሪዎች ስምሪት በምልልስ ለመስጠት 189,996 ታቅዶ 166,625 የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀሙ በፐርሰት ሲሰላ 87.6% ነው፣

ከመናኻሪያ አገልግሎትና ከትራንስፖርት ደንብ ተላላፊ (ያለመስመር ማሽከርከር ፣ያለመንጃ ፍቃድ ማሽከርከር ፣ያለስምሪት መንቀሳቀስ ፣ያለቦታመቆም፣ትርፍሰው መጫን፣ቦሎእና 3ኛወገን አለመለጠፍ የመሳሰሉት) ገቢ ለመሰብሰብ በብር 5,968,388 ታቅዶ 4,255,391 የተገኘ ሲሆን አፈጻጸሙም በፐርሰንት ሲሰላ 71.2%ተከናውኗል፡፡

## በዕቅድ የስራ ሂደት የተከናወኑ ስራዎች፣

- ◈ የመረጃ መሰብሰቢያ ፎርማት ማዘጋጀት፣ ስለመረጃ አያያዝና አጠቃቀም ለፈጻሚ አካላት በቂ ግንዛቤ እንዲፈጠር ተደርጓል፣
- ◈ በአፈጻጸም ግምገማ ውሳኔ የሚያስፈልጋቸውን ተግባራት በመለየት ለመመሪያው ማንጅመንት ለማቅረብ 40 ታቅዶ 36 የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙ በፐርሰንት ሲለካ 90% ተከናውኗል፡፡
- ◈ ክፍተቶችን በመለየት የማጠናከሪያ ሥራዎች በመሥራት፣ የባለድርሻ አካላትና ተገልጋዮች የጋራ ምክክር መድረክ ለማካሄድ 50 ታቅዶ 46 የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙ 92% ተከናውኗል፡፡

◈ የረጅም፣ የመካከለኛና የአጭር ዓመት (የ10፣ የ5 እና የአንድ ዓመት) ዕቅዶችን እንዲሁም የ2015 ዓ.ም የበጀት ፍላጎት ዕቅድ በማቀድ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡

**ከእቅድ ውጭ የተሰሩ ስራዎች፡**

- ያጋጠመንን እጥረትና አቅርቦት በግዚያዊነት ለመቅረፍ ሲባል መምሪያው በመነኸሪያ ውስጥ ያሉ የህዝብ ትራንስፖርት ማህበራት እና የከተማ ታክሲ ማህበራት ጋር በመወያየትና የጋራ ስምምነት ጋር በመድረስ ለክልሉ ንግድ ቢሮ በማሳወቅ ከአጎራባች ክልሎች ከአማራና ከኦሮሚያ ክልል 266,560 ሊትር ናፍጣና 230,620 ሊትር ቤንዚል በማስመጣት ስርጭት ተደርጓል
- ባለሀብቶችን በማስተባበር ሁለት ተርሚናል ሩም/ሼድ ለታክሲ ተጠቃሚ ለሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች ማረፊያ ተሰርቷል፡፡

ስትራቴጂክ የልማት ዕቅድ ዘመን በግብርና ምርት ግብይት ዘርፍ በርካታ ስራዎች የተሰሩ ቢሆንም በቀጣዩ ዕቅድ ዘመናችን ትኩረት የሚሹ በርካታ ተግዳሮቶች ተስተዉሏል፡፡ ከተግዳሮቶቹ መካከል ከፍተኛ መጠን ያለው የኤክስፖርት ምርት ወደ አጎራባች ክልሎች በህገወጥ መንገድ መዉጣቱ፣ መዋቅሩ በሚፈለገው የሰው ሀይል እና ቴክኖሎጂ አለመደራጀቱ፣ የባለድርሻ አካላት የትብብርና ቁርጠኝነት አናሳ መሆን፤ የተጀመሩ የግብይት ማእከላት አለመጠናቀቃቸዉ፣ ከመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማእከላት ውጭ ግብይት መፈጸምና በሕገ ወጥ መንገድ ግብይት መኖሩ፣ የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ገበያ ማዕከላት በተጠናከረ መልኩ ያለመደራጀትና ዘመናዊ ግብይት ሥርዓት ዉስጥ ገብቶ ግብይት ያለመፈፀማቸዉ ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ በቀጣዩ ዕቅድ ዘመን በዚህ ዘርፉ ሊገኝ የሚችለዉን ምርት በጥራት እና ህጋዊ ግብይት ስርዓት በመዘርጋት የከተማችን ህብረተሰቡ ተጠቃሚ እንዲሆን እንደ አንድ መነሻ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

በእቅድ ዘመኑ የበጀት እና የተሽከርካሪ እጥረት መኖር፤በሁሉም ደረጃ ያሉት ግብረ-ሀይሎች ተቀናጅቶ ያለመስራት፤የክትትል ስራዎች በቅንጅት እና ውጤት ማምጣት በሚችል መልኩ አለመሆኑ፤ዘርፉ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ አለመደገፍ፤አዳዲስ ኢንዱስትሪዎች ወደ ልማት እንዲገቡ እና ነባሮች በሚፈለገዉ መልኩ እንዲጠናከሩ ለማስቻል የመስርያ ቦታ ችግር መኖሩ ያጋጠሙ ክፍተቶች ሲሆን ክፍቶችንም ለመቅረፍ ያለዉን በጀት በቁጠባ በመጠቀም፤ለተቋቋሙ አደረጃጀቶች እና ግብረ ሀይሎች የአቅም ማጎልበቻ ስልጠና በመስጠት ወደ ስራ እንዲገቡ በማድረግ ችግሩ በተወሰነ መልኩ ለመቅረፍ ተችሏል፡፡

### 2.2.የዘርፉ ተግዳሮቶች (Identified Challenges)

1) ህገወጥ ንግድና ኮንትሮባንድ መስፋፋት

- ህጋዊ የሆኑ ነጋዴዎችን አቅም ማዳከምና ከውድድር ውጭ እንዲሆኑ ማድረግ፣
- አላስፈላጊ የምርት ክምችትና የአቅርቦት እጥረት በመፍጠር በኑሮ ውድነት ላይ ጫና መፍጠሩ፣
- ህጋዊ ነጋዴዎችን የሚያበረታታ ስርዓት አለመፈጠር
- ህገ-ወጥ ንግድ መበራከት
- ጅምላ ነጋዴዎች ለቸርቻሪ ነጋዴዎች የሚሸጡትን እቃ የለደረሰኝ መሸጥ
- አንዳንድ ነጋዴዎች ፈቃደኛ ሆነው አስፈላጊ መረጃ አለመስጠት
- አንዳንድ ነጋዴዎች ድርጅታቸውን ዘግተው መጥፋት
- አብዛኞቹ ነጋዴዎች የሚሸጡበትን ዋጋ ዝርዝር ያለመለጠፍ
- ለስምሪት የወጡ ባለሙያዎች ወጣ ገባ ማብዛት
- ነጋዴዎች የኮትሮባንድ ንግድ ሀገርን እንደሚጎዳ ግንዛቤ ማነስ
- የነጋዴ ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ከመምሪያውና ግብረ-ኃይሉ ጋር በጋራ አለመስራት
- የተጠያቂነት አሰራር አለመጠናከር
- መሠረታዊ የፍጆታ እቃዎች ወቅቱን ጠብቆ ያለመምጣት ምሳሌ ስኳርና ዘይት እንዲሁም የነዳጅ እጥረት መኖሩ
- የማደያ ባለቤቶች ለኢንስፔክሽን በሚካሄድበት ወቅት ፍቃደኛ ያለመሆን

2) **ህገወጥ ተሸከርካሪ አሽከርካሪዎች መበራከት**

- አሽከርካሪዎች ትርፍ ሰው መጫንና  የትራፊክ ደንቦችን ያለማክበር ችግር
- አሽከርካሪዎች  ማሟለት ያለባቸውን መስፈርቶችን አሟልቶ ያለማሽከረካር
- ህጋዊ አሰራርን ለማጠናከር በሚደረገው እንቅስቀሴ ወቅት አሽርካሪዎች መብታቸውን እንጂ ግዴታቸውን ጠንቅቀው ያለማወቅ ችግር
- ሶስተኛ ወገን እና ቦሎ ሳያሳድሱና ሳይለጥፉ የሚያሽከርክሩ አሽከርካሪዎች መበራከት
- የበጀት  እጥረት በመኖሩ ስራዎችን በቅንጅት መስራት እንቅፋት መሆኑ
- ስራዎችን ለመከታተል የተሸከርካሪ እጥረት መኖሩ
- አዳዲስ  አሰራርና ፈጠራዎችን የማመንጨት ዉስንነት፣
- የጥፋተኛ አሽከርካሪዎች መረጃ አያያዝ መተግበር ውስንነት መኖሩ፣
- ሀገር አቀፍ የተቀናጀና በቴክኖሎጂ የታገዘ የቁጥጥር ስራ በዘላቂነት አለመቀጠሉ

3) **የኢንዱስትሪ ግብዓት አቅርቦት ችግር**

- ለአግሮ ፕሮሲሰንግ ኢንዱስትሪ ግብዓት የሚውሉ የግብርና ግብዓቶችን ማምረት የሚያስችሉ እምቅ ሀብት ያላት ቢሆንም እነዚህን ግብዓቶች በሚፈለገው ጥራት፣ ዋጋ፣ መጠንና ጊዜ ለኢንዱስትሪው ማቅረብ አልተቻለም፤
- የማምረቻ እና የመሸጫ ቦታ የማቅረብ ችግር
- የመሰረተ ልማት ችግር(ኤሌክትሪክ፤ዉሀ እና መንገድ)
- ክህሎት ያለዉ የሰለጠነ የሰዉ ሀይል ዉስንነት

4) የማንጅመንትና የቴክኖሎጂ አቅም ውስንነት

- ያሉት አነስተኛ እና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ዘመናዊ የሥራ አመራርና የጥራት ስራ አመራር ሥርዓት የተጠናከረ አለመሆን፤
- ዝቅተኛ ምርታማነት (ኢንዱስትሪው ከአቅም በታች ማምረት፣ ዝቅተኛ የሠራተኛ ምርታማነት፣ የሰው ኃይል አለመረጋጋት)፤
- የኢንዱስትሪ - ዩኒቨርስቲ፣ የምርምርና ቴክኒክና ሙያ ተቋማት ትስስር አለመጠናከር፤
- የጥራት መሠረተ ልማት በአምራች ኢንዱስትሪው ያለመስፋፋት፣

5) የመንግስታዊ ተቋማት የአገልግሎትና ድጋፍ አሰጣጥ ቀልጣፋና ውጤታማ አለመሆን
- የሚሰጡ የድጋፍ አገልግሎቶች በሚጠበቀው ደረጃ ቀልጣፋና ውጤታማ ያለመሆን፤
- በኢንዱስትሪዎች የሚከሰተው የኤሌክትሪክ ኃይል መዋዠቅ፣ መቆራረጥና የአቅርቦት ችግር፤
- መንግስታዊ ተቋማት ተቀናጅተው አለመስራት፤
- በመንግስት የሚሰጡ የማበረታቻ ድጋፎች (ብድር) በትክክል ለታለመላቸው ዓላማ ስለመዋላቸው የመከታተል ውስንነት፤
- የፋይናንስ ድጋፍ በተገቢው ሁኔታ ያለመፈፀም፣ የሎጀስቲክስ አቅርቦት ክፍተት እና የመሬት አቅርቦት በዋናነት የሚጠቀሱ ተግዳሮች ናቸው፡፡

## 2.3. ለዘርፉ ልማት ወሳኝ የሆኑ ሰብዓዊና ቁሳዊ ሀብቶች

ለንግድና ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ወሳኝ የሆኑ ሰብዓዊና ቁሳዊ ሀብቶች በዋናነት፡-

- ለቀላል ኢንዱስትሪ ልማት ሊውል የሚችል ግብዓት (ጥጥ ፣ የእንስሳት ሀብት፣ ጥሬ ቆዳና ሌጦ ፣ ወዘተ…) በስፋት መኖሩ፣
- ለከባድ ኢንዱስትሪ ልማት የሚውል ግብዓት (የድንጋይ ከሰል፤እምነ በረድ) መኖሩ፤
- የንግድ ሥርዓቱ ለማዘመን እየተከናወነ ያለው የሪፎርም ሥራ፤
- ዘመናዊ የግብይት ማዕከላት እየተስፋፋ መምጣቱ፤
- ወጣት እና በአጭር ጊዜ ስልጥኖ ወደሥራ ሊሰማራ የሚችል የሰው ሃይል መኖሩ፣
- የኢንዱስትሪ ፓርክ ግንባታ ቦታ ርክክብ ጅምር  መኖሩ፤
- ለአነስተኛ ኢንዱስትሪዎች ፋይናንስ የሚያቀርቡ ተቋማት መኖራቸው፤
- የዘርፉ እውቀት፣ ክህሎት እና የረጅም ዘመን የሥራ ልምድና ተነሳሽነት ያላቸው ባለሙያዎችና አመራሮች
- የህዝብ ትራንስፖርት መናኻሪያዎች፣ የህዝብ ትራንስፖርት አቅራቢ ማህበራት እና ተሸከርካሪዎች  መኖር
- በመንገድ ትፊክ ደህንነት ዙርያ ግንዛቤ በመፈጠሩ የትራፊክ አደጋ መቀነሱ
- በክልል፣ በመምሪያ ፣ በወረዳ እና በትራፊክ ፖሊሶች ጋር በመሆን በመንገድ ደህንነት ዙርያ ቅንጅታዊ አሠራር መፈጠሩ

**ምዕራፍ ሦስት፤**

## 3. የዕቅዱ ዓላማ፤ግቦችና የትኩረት አቅጣጫዎች

### 3.1. የዕቅዱ ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮች

1. የላቀ የንግድ ስርዓት ማስፈን
2. ዘመናዊ የግብርና ምርቶች ግብይት ማስፋፋት
3. የኢንዱስትሪ ልማትን ማሳደግ
4. የላቀ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት
5. የላቀ የመፈጸምና የማስፈጸም አገልግሎት

## 3.2.የእቅዱ ዓላማዎች

- የንግድ ምዝገባና የንግድ ስራ ፈቃድ በመስጠት ፣በንግድ ድርጅቶች ላይ የክትትልና ቁጥጥር ስርዓት በማጠናከር ፣የተረጋጋ የገበያ ስርዓት በማስፈን፣መሰረታዊ ፍጆታ ዕቃዎች ስርጭት ፍትሃዊ በማድርግ፣ህጋዊ የስነ-ልክ መሳሪያ ቨሪፊኬሽን መስራት ላይ ያለመ ይሆናል፣
- የግብይት መሰረተ-ልማት፣ወቅታዊ የገበያ መረጃዎች፣የገበያ ትስስር፣የህገ-ወጥ ንግድና ጥራት ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ
- አምራች ኢንዱስትሪዎችን በማስፋፋት የማምረት አቅማቸዉን ማሳደግ
- አስተማማኝና ደህንነቱ የተጠበቀ ፍትህዊ የህዝብና የጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት ተደረሽነትን ማረጋገጥ
- የመ/ቤቱን የሰው ሀይል በማሟለት፣የአጭርና የረጅም ስልጠና በመስጠት፣ የመረጃ አየያዝና የቴክኖሎጂ አቅም በማሰደግ የመፈጸምና የማስፈጸም አቅምን ማሳደግ

## 4.የዕቅዱ ግቦች

ግብ-1 የንግድ ምዝገባና የንግድ ስራ ፈቃድ እድሳትና አሰጣጥ ኢንስፔክሽን ማካሄድ፣

ግብ-2 በንግድ ድርጅቶች ላይ የተጠናከረ አንስፔክሽን/ የቁጥጥርና ክትትል ማድረግ

ግብ-3 የተገልጋይ እርካታ ማሳደግ

ግብ-4 የመለኪያ መሣሪያዎች ቬሪፋ ማድረግ/ ማረጋገጥ

ግብ-5. ፍትሀዊ የመሰረታዊ የፍጆታ ዕቃዎች ስርጭት እንዲኖር ማደረግ

ግብ-6 ፍትሀዊ የንግድ ውድድር ማስፈን

ግብ-7 ዘመናዊ የመረጃ አጠቃቀም ስርዓት ማሳደግ

ግብ-8 ዘመናዊ የግብይት ስርዓት

ግብ-9 በግብይት ዘርፍ አሰራር አደረጃጀት ማሻሻል

ግብ-10 የኢንዱስትሪ ልማት ማሳደግ

ግብ-11 የአምራች ኢንዱስትሪዎችን በማስፋፋት አቅም ማሳደግ

ግብ፡12 የህብረተሰቡን የመንገድ አጠቃቀም ግንዛቤ ማሳደግ

ግብ፡-13 የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ተደራሽነትን ማሳደግ

.

.

### 5.የዕቅዱ የትኩረት አቅጣጫዎች

- በየደረጃው የመፈጸም እና የማስፈጸም አቅምን ማሳደግ፤
- የዘርፉን እድገት ማሳለጥ የሚያስችሉ የቅንጅታዊ አሰራሮችን ማጠናከር፤
- ዘመናዊ የመረጃ አጠቃቀም ስርዓትን ማሳደግ
- ቀልጣፍ የንግድ አሰራሮችን ለማዘመን የሪፎርም ሥራዎችን አጠናክሮ ማስቀጠል፤
- የወጪ ንግድ የምርት መጠን፣ ስብጥር እና ጥራትን ማሳደግ፤
- ዘመናዊ የግብይት ሥርዓት በመዘርጋት፣የምርትና አገልግሎቶችን ጥራትና ደህንነትን የማረጋገጥ ስራዎችን አጠናክሮ በማስቀጠል የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፤
- የመጀመሪያ እና የሁለተኛ ደረጃ የግብይት ማዕከላት ግንባታ ማስፋፋት፤
- የሸማቹን መብት እና ደህንነት በማስጠበቅ የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ
- የነባር ኢንዱስትሪዎች ምርትና ምርታማነትን የማሳደግ ስራ አጠናክሮ ማስቀጠል፣
- የአገር ውስጥ ግብዓቶችን ለሚጠቀሙ የማኑፋክቸሪንግ አምራቾች ቅድሚያ መስጠት፤
    - የአምራች ኢንዱስትሪውን የእሴት ሰንሰለት፣ትስስርና ተመጋጋቢነትን ማጠናከር፤
    - በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ አዳዲስ ኢንቨስትመን በጥራት እና በአይነት ማስፋፋት፤
    - የኢንዱስትሪ ክላስተር ግንባታ በማከናወን የህበረተሰቡን ተጠቃሚነት ማሳደግ
    - የክላስተር አደረጃጀትን በማጠናከር እና የአነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎችን በማስፋፋት የዘርፉን የሥራ ዕድል ፈጠራ አቅም ማሳደግ እና በሂደት ወደ ቀጣይ ደረጃ የሚሸጋገሩበትን አቅጣጫ መከተል፤
    - የግሉን ዘርፍ ሚና እና አጋርነት ማሳደግ፣
    - ለማህበረሰቡ ግንዛቤ በመፍጠርና የህዝብ ንቅናቄ በማጠናከር፣ የቅርብ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ የትራፊክ አደጋን መቀነስ
    - የመናኻሪያዎችን ደረጃ በማሰጠበቅ የሚታዩ ችግሮችን በመለየትና በመፍታት የተሻለ የትራንስፖርት አገልግሎት ህብረተሰቡ እንዲያገኝ ማድረግ
    - ከአጎራባች ክልሎችና ወረዳዎች ጋር በመቀናጀትና በጋራ በመስራት አዋሳኝ አካባቢ ያለውን የትራንስፖርት እንቅስቃሴ የተፋጠነ እንዲሆን ማድረግ
    - የጥፋተኛ አሽከርካሪዎች መረጃ አያያዝ እንዲተገበር ማድረግ፣
    - ሀገር አቀፍ የተቀናጀና በቴክኖሎጂ የታገዘ የቁጥጥር ስራ እንዲጀምር ማድረግ
    - የትራንስፖርት ማንጅመንት ስርዓት መዘርጋት፣
    - የመንገድ ትራፊክ ደህንነትን ማረጋገጥ ፣

- የመናኻሪያ አስተዳደር ስርዓት ማሻሻል፣

## 5.1 .የማስፈጸሚያ ተቋማዊ አቅም፤ ፖሊሲና ስትራቴጂዎች

- የንግድ ምዝገባ ፍቃድ አሰጣጥ አዋጅ
- የፖሊሲና ስትራቴጂ አዋጅ፤
- የንግድ ዉድድር እና የሸማቾች ጥበቃ አዋጅ
- የመሰረታዊ ፍጆታ ስርጭት ደንብ
- የቡና ፤የቆዳና ሌጦ እና ቁም እንስሳት አዋጅ
- በትግበራ ላይ ያለው የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ፤
- የመንገድ ትራንስፖርት ፖሊሲ፣ደንብና መምሪያዎች
- የዘርፉን የአደረጃጀት ማሻሻያዎች
- የብዙሃን ትራንስፖርት ማስፋፊያ ስትራቴጂ
- የመምሪያው ትራንስፎርሜሽን ኢኒሺዬቲቭ
- ሌሎች ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች፤

## 5.2.መልካም አጋጣሚዎች እና ስጋቶች

### 5.2.1.መልካም አጋጣሚዎች /አስቻይ ሁኔታዎች / enablers/

- የአገሪቱ የፖለቲካ ፤ የዲሞክራሲ፣ የሰላምና መልካም አስተዳደር ሁኔታ እየተሻሻለ የመጣ መሆን፤
- ሕብረተሰቡን በየደረጃዉ ተጠቃሚ ሊያደርጉ የሚችሉ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጅዎችና አሰራሮች መኖር፣
- ልማቱን ለማፋጠን የሚያስችሉ መሰረተ ልማቶች ዝርጋታና ማህበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እየተስፋፋ መምጣት፣
- የህብረተሰቡ የስራ ባህል እያደገ መምጣት፣
- አዳዲስ ቴክኖሎጅዎች ገበያ ላይ መኖርና የመጠቀም ልምድ እያደገ መምጣት፣
- የአገልግሎት አሰጣጥና የአገልጋይነት ስሜት እየተሻሻለ መምጣቱ፣
- የሰራተኛዉ የስራ ተነሳሽነትና የዉሳኔ ሰጭነት ባህል እየዳበረ መምጣት፣
- ሂደቱን ለማብቃት የሚደረግ ጥረት መኖር፣
- አመራሩ መንግስት የሚያወጣቸው የተለያዩ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ለመተግበር የለውጥ ዝንባሌ መኖር፣

- በዕቅድ መመራት እየጎለበተና በየሳምንቱ አፈፃፀምን በማነጅመንት እየገመገሙ የመሄድ ጅምሮች መኖር፣
- ቀጣይነት ያለዉ የከተማ እድገት የኢኮኖሚ እድገት መመዝገቡ
- በንግድና ኢንቨስትመንት የመስማራት ፍላጎት እያደገ መምጣቱ/የሥራ ባህል/፣
- ለእርሻ ኢንዱስትሪና ለሌሎች ልማቶች ምቹ ሥነ-ምህዳር መኖሩ፤

5.2.2.ስጋቶች/ ፈታኝ ሁኔታዎች /Pains/

- የለዉጥ አቅጣጫዎችን በቀጣይነትና በተሟላ ሁኔታ አለመተግበርና ዉጤታማነቱንም አለመለካት፣
- በአመራሩና በፈጻሚዉ የአመለካከት፣ የክህሎት፣ የተነሳሽነት ውስንነት፣
- ኪራይ ሰብሳቢነትን በቀጣይነትና በፅናት ያለመታገል፣
- አዳዲስ  አሰራርና ፈጠራዎችን የማመንጨት ዉስንነት፣
- በመጠን በጥራትና በዋጋ ተወዳዳሪ የሆነ ምርትና አገልግሎት አለመቅረብ፣
- የአፈጻጸም መረጃዎችን አደራጅቶ አለመያዝና በአግባቡ ለተጠቃሚ አለማድረስ፣
- የሰዉ ሀይል የመፈጸም ብቃቱን በዉጤት አለመለካትና የማበረታቻ ስርዓት አለመዘርጋት፣
- በአደረጃጀት የተግባራት መደበላለቅ መኖር፣
- ከክልል እና ከተማ አስተዳደሩ ጋር ያለዉ ተቋማዊ ግንኙነትና ቅንጅታዊ አሰራር በሚጠበቀዉ ደረጃ አለመሆን፣
- የሸቀጥና የአገልግሎት ዋጋ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መሄድ፣
- ህገ ወጥ ንግድና ኋላ ቀር የግብይት አሰራር መስፋፋት፣
- ህብረተሰቡ በተደራጀ አግባብ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮቹን ለመፍታት የሚያደርገዉ ጥረት አነስተኛ መሆን፣
- ለልማት ተፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችንና መሰረተ ልማቶች በበቂ መጠን፣ በተመጣጣኝ ዋጋና በወቅቱ ያለመቅረብ፣
- በህብረተሰቡ ዉስጥ ያለዉ የጠባቂነት፣ የተረጅነትና የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከት ያልተቀረፈ መሆን፣
- ቴክኖሎጂን በመገልገል የመፈጸም አቅም ውስንነት መኖር፣
- ለሴቶችና ወጣቶች የሚሰጠው ትኩረት አናሳ መሆን
- ለተገልጋይ ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት አለመስጠት

- ግልጸኝነትና ተጠያቂነት ያለመኖር
- መሰረታዊ ፍጆታ ኮታ ከህዝብ ቁጥር ጋር ያለመጣጣም
- ክልሉ ጠረፋማ ከመሆኑ አንፃር አልፎ አልፎ ያለመረጋጋት ሊኖር ይችላል፣
- ለኢንዱስትሪ ልማት ስራዎች በቂ በጀት እና መሰረተ ልማት ላይሟላ ይችላል

### 5.2.3. የስጋት ማስወገጃ ስልቶች፣

- መልካም አጋጣሚዎች አሟጦ በመጠቀም ስጋቶች የሚፈጥሩት ተፅዕኖ ለመቀነስ ቀጥሎው የተዘረዘሩት ስልቶች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡
- የለዉጥ አቅጣጫዎችን በቀጣይነትና በተሟላ በመተግበር ዉጤታማነቱን መለካት፣
- በፈጻሚዉ የአመለካከት፣ የክህሎት፣ የተነሳሽነት ውስንነትን ማስወገድ
- ኪራይ ሰብሳቢነትን በቀጣይነትና በፅናት መታገል፣
- አዳዲስ አሰራርና ፈጠራዎችን የማመንጨት ፤
- ቴክኖሎጂን በመገልገል የመፈጸም አቅም ማሳደግ፣
- ዘመናዊ የግብይት ስርዓትን በማጠናከር ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ምርቶች ዓይነትና ብዛት በመጨመር ወደ ግብይት ስርዓት ያልገቡ የግብርና ምርቶች እንዲገቡ ማድረግ፤
- ከከተማው ህዝብ ቁጥር ጋር የተጣጣመ የመሰረታዊ ፍጆታ እንዲላክ ጥያቄ ማቅረብና ክትትል ማድረግ
- የግብርና ምርቶች እሴት ጨምረው ለውጭ ገበያ እንዲቀርቡ ማድረግ እና ለውጪ ገበያ የሚቀርቡ የኢንዱስትሪ ምርቶች ተገቢውን ትኩረት ሰጥቶ መስራት፤
- የመፈፀምና የማስፈፀም ውስንነት ለመፍታት ቅንጅት ስራዎችን አጠናክሮ መቀጠል፡፡
- የመሠረተ ልማት እና ተያያዥ አገልግሎቶች ላይ የሚታየውን ክፍተቶች ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት ለመፍታት ይሞከራል፡፡
- ከግብርና የኢንዱስትሪ ግብዓቶች ጋር በተያያዘ የአግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ ትግበራን በማቀላጠፍና ከግብርና ዘርፍ ጋር የቅንጅት ስራ በማሳለጥ ለመፍታት ይሠራል፡፡

.

## 6.. የአፈጻጸም ሪፖረት፣ ክትትልና ግምገማ

የ10 ዓመቱ መሪ ዕቅድ መሰረት በማድረግ በሚፀደቀው ዓመታዊ ዕቅድ የሥራ ኃፊላዎች በየጊዜው የቅርብ ክትትል እየተደረገ፣ ወርሃዊ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት እንዲዘጋጅ ተደርጎ በየተቋማቱ የበላይ አመራር ሰብሳቢነት በሥራ አመራር ደረጃ ይገመገማል፡፡

### 6.1 የሪፖርት አቀራረብ፤

ከበጀት ዓመቱ ዕቅድ አኳያ ከተቀመጡ ግቦች አንጻር የግምገማ ሪፖርት ሲዘጋጅ የዘርፍ ቁልፍ አፈፃፀም የውጤት አመልካቾች (Output Indicators) እና የስኬት አመልካቾች (Outcome Indicators) ታሳቢ ባደረገ አግባብ የሚፈፀም ሆኖ የሪፖርት አቀራረብ ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

| የዘርፉ መጠሪያ | የስራው ባለቤት መጠሪያ | |
|---|---|---|
| የሚሰበሰቡ መረጃዎች የሚሸፍኑት ጊዜ | የሪፖርቱ ይዘት | ሪፖርቱ የሚቀርብለት አካል |
| አመታዊ | ስኬቶች እና ውጤቶችን ያካትታል፡፡ በተጨማሪም ዘርፈ ብዙ ጉዳዮችን፣ የበጀት ውጤታማነትንና የኦዲት እና የለውጥ፣ የመልካም አስተዳደርና የሰው ሀ/ስ/አመራር ጉዳዮችን ማካተት አለበት፡፡ | ለክልሉ ንግድ እና ኢንዱስትሪ ቢሮ ፤ ለክልሉ ገጠር መንገድ ትራንስፖርት ቢሮ፣ ለአሶሳ ከተማ አስ/ርም/ቤት፣ ገ/ኢ/ል/መምሪያ፣ከንቲባ ጽ/ቤትና ለብልጽግና ፓርቲ |
| ስድስት ወራት | ለስኬቶች እና ውጤቶችን ያካትታል፡፡ በተጨማሪም ዘርፈ ብዙ ጉዳዮችን፣ የበጀት ውጤታማነትን፣ የኦዲት እና የለውጥ፣ የመልካም አስተዳደርና የሰው ሀ/ስ/አመራር ጉዳዮችን ማካተት አለበት፡፡ | ለክልሉ ንግድ እና ኢንዱስትሪ ቢሮ ፤ ለክልሉ ገጠር መንገድ ትራንስፖርት ቢሮ፣ ለአሶሳ ከተማ አስ/ር ም/ቤት፣ ገ/ኢ/ል/መምሪያ፣ከንቲባ ጽ/ቤትና ለብልጽግና ፓርቲ |
| በየሩብ ዓመት | ለስኬቶች እና ውጤቶችን ያካትታል፡፡ በተጨማሪም ዘርፈ ብዙ ጉዳዮችን፣ የበጀት ውጤታማነትን፣ የኦዲት እና የለውጥ፣ የመልካም አስተዳደርና የሰው ሀ/ስ/አመራር ጉዳዮችን ማካተት አለበት፡፡ | ለክልሉ ንግድ እና ኢንዱስትሪ ቢሮ ፤ ለክልሉ ገጠር መንገድ ትራንስፖርት ቢሮ፣ ለአሶሳ ከተማ አስ/ር ም/ቤት፣ ገ/ኢ/ል/መምሪያ፣ከንቲባ ጽ/ቤትና ለብልጽግና ፓርቲ |

የዘርፉ የሩብ ዓመት፣ የግማሽ ዓመት፣ የዘጠኝ ወራትና ዓመታዊ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶችን በማዘጋጀት በዘርፉ የበላይ አመራር ሰብሳቢነት ሥራ አመራር እና በጠቅላላ ሠራተኛ እንዲገመገም ይደረጋል፡፡ ከዚያም የከተማ አስ/ሩ ቋሚ ኮሚቴ ላይ ቀርቦ ግምገማ የሚደረግ ሲሆን የሚሰጡ ግብረ-መልሶች እና የሥራ አቅጣጫም ተግባራዊ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ በየሩብ ዓመቱ ከተቋሙ የሱፐርቪዥን ቡድን በማቋቋም በከተማ አስተዳደር ስር ባሉ ወረዳዎች ክትትል እና ግምገማ በማድረግ ግብረ መልስ መስጠት

### 6.1.2. የግምገማ መድረኮች

በዘርፉ የሚዘጋጀው ሪፖርት ከላይ የተጠቀሱትን የአመልካች አይነቶችን ታሳቢ በማድረግ ግምገማው የሚያተኩርባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች፡-

የዘርፉ የፊዚካል አፈፃፀም፣

የባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን ማለትም፡- የስርዓተ-ፆታ ፣ የወጣቶች እና የሴቶች፣ ኤች አይ ቪ/ኤድስ፣ አካል ጉዳተኞች እና የአየር ንብረት ለውጥን

የዘርፉ የበጀት አፈፃፀም፣

የዘርፉ ኦዲት አፈፃፀም፣

የተቋማዊ ለውጥ፣ መልካም አስተዳደር እና ሰው ሀብት ስራ አመራር አፈፃፀም፣

ላይ በማተኮር የዘርፉ ቁልፍ የውጤት መስክ ለማሳካት የሚከናወኑ ቁልፍ ተግባራትን አፈጻጸም ለመከታተልና ለመገምገም በሚያስችል አግባብ የዘርፉ የበላይ አካልም ሆነ በየደረጃው ያለ አመራር ይህንኑ ታሳቢ በማድረግ ተግባር ነክ አመልካቾች ላይ የቅርብ ክትትል በማድረግና የሚያጋጥሙ ማነቆዎችን በመፍታት ለቁልፍ የውጤት መስኮች ያላቸውን አስተዋፆ በማሳደግ ውጤታማና ተፈፃሚ መሆናቸውን በማረጋገጥ ግምገማው የሚከናወን ይሆናል፡፡

የግምገማ መድረኮች አንደኛ በማንጅመንት ደረጃ በየ2ሳምንት አንድ ጊዜ ውይይት እየተደረገ የስራዎች አፈጻጸም ደረጃ፣ ያጋጠሙ ችግሮች እና ስለሚወሰደው ማስተካከያ እርምጃ ይወሰናል ማለት ነው፡፡ በመምሪያ ደረጃ በአመት ሁለት ጊዜ በስድስት ወር ላይ እና በአመቱ ማለቂያ በአፈጻጸም ሪፖርቱ ዙሪያ አጠቃላይ ሰራተኛ ባለበት ውይይት ይደረጋል፡፡

### 6.1.3. የመስክ ክትትልና ቁጥጥር ስራዎች

በክትትልና ግምገማ ዕቅድ መሰረት ቼክ ሊስት እየተዘጋጀ መስክ ላይ የሚከናወኑ ስራዎች በአካል በመገኘት ቁጥጥር ይደረጋል፡፡ በዚህም መሠረት ስራው ከዕቅዱ አንጻር የደረሰበት ደረጃ፣ ጥራቱ ወዘተ ቁጥጥር እየተደረገ አስፈላጊው ማሻሻያ ይደረገል፡፡

### 6.1. 4 የዕቅዱ ማስፈፀሚያ ዋና ዋና ስልቶች/ IMPLEMENTATION STRATEGIES

**ሀ.ሁሉን አቀፍ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን አጠናክሮ ማስቀጠል፤**

የዘርፉን አሠራርና አደረጃጀት ማጠናከር (የኢንዱስትሪ፣ የወጪ ንግድ)፤

የሰው ኃይል ልማት፤

የተቋማት ቁርኝት ትግበራ ማጠናከርና ማስፋፋት፤

**ለ.የምርት፣ምርታማነት፣ ስብጥርና ጥራት ማሻሻያ በስፋት ማከናወን፤**

የጥራት ደረጃውን ያሟላ፣ ያልተቆራረጠ፣ በቂና ፈጣን የምርት ግብዓት አቅርቦትን ማረጋገጥ፤

አዳዲስ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ልማት፤

የካይዘን ሥራ አመራር ፍልስፍና፣ የጥራት ሥራ አመራር (QMS)፣ የቤንችማርኪንግ፣

የኢንዱስትሪ-ዩኒቨርስቲ/ቴ.ሙ.ተ. ትስስር፤

የሥራ አመራርና የቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ፤

**ሐ.የንግድ አሠራር ምቹነት (easy of doing business) ሪፎርም ሥራዎች ማጠናከር፤**

የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎትን ማዘመን፤

በጥናት ላይ የተመሠረተ የግብይት ሰንሰለት ለማሳጠር የሚያስችል የግብይት ሰንሰለት ሪፎርም፤የጥራት ኢስፔክሽንና ሬጉላቶሪ ስራዎችን ሪፎርም፤

**መ. ኢንቨስትመንት ማስፋፋት፤**

በኮንስትራክሽን፣በንግድና አገልግሎት ዘርፍ የተሠማሩ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን ወደ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ማስገባት፤

የተቀናጀ የአግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርክ ልማት፤

የአነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪ ክላስተር ልማት፤

ሠ.አስተማማኝና ዘመናዊ የንግድና ኢንዱስትሪ መረጃ ሥርዓት መገንባት፤

ረ.በጥናት ላይ የተመሠረተ የማበረታቻ ሥርዓት፣ ዘመናዊ የምርት ማቆያ፣ የማዘጋጃና የግብይት ማዕከላት ማስፋፋት

➢ <u>በአሶሳ ከተማ አስ/ር ወረዳ ሁለት ንግድ ኢንዱስትሪ ትራንስፖርት ጽ/ቤት ስትራቴጂክ **የተከለሰ** የልማት**ዕቅድ(ከ**</u>2015(1/2) - -2017(1/2) **እቅድ**

| የተቋሙ ስትራቴጂያዊ ግብ5 | ክብደት | የግብ ተኮተግባራት | ክብደት | መለኪያ | ከ2013---- ታህሳስ 30 2015 አፈፃፀም መነሻ | ዓመታዊ ዒላማና አፈፃፀም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | የ2015(1/2) ዒላማ | የ2016 ዓመት ዒላማ | የ2017 ዓመት ዒላማ |
| ግብ 1 የተገልጋይ እርካታ ማሳደግ | 5 | ተገልጋይ በተቋሙ በሚያገኙት አገልግሎት 85 በመቶ እንዲረኩ ይደረጋል | 0.5 | የተፈታ አቤቱታ በመቶኛ | 62.8 | 63 | 66 | 70 |
| | | የተገልጋይ እርካታ ደረጃ ለማረጋገጥየዳሰሳ ጥናት ማድረግ | 3 | የተደረገ ዳሰሳ ጥናት በሰነድ | - | 2 | 4 | 5 |
| | | የቀረቡ.አቤቱታዎችን በመቀበል መፍታት | 0.5 | የረካ ተገልጋይ በመቶኛ በመቶኛ | 0 | 60 | 70 | 100 |
| | | ከተቋሙ አገልግሎቶች ገቢ መሰብሰብ | 1 | ከንግድ ስራ ፍቃድ አገልግሎት ገቢ መሰብሰብ በብር | 917,139 | 1,500,000 | 1,800,000 | 1,900,000 |
| ግብ:2 ፍትሀዊ የንግድ ውድድርን ማስፈን፤ | 5.2 | አዲስ የንግድ ምዝገባ ፍቃድ አገልግሎት መስጠት ፤ | 0.6 | አዲስ የንግድ ምዝገባ ፍቃድ መስጠት በቁጥር | 199 | 1000 | 1100 | 1200 |
| | | አዲስ የንግድ ስራ ፍቃድ አገልግሎት ለመስጠት | 0.4 | አዲስ የንግድ ስራ ፍቃድ መስጠት በቁጥር | - | 1,100 | 1200 | 2,000 |
| | | ምትክ ንግድ ስራ ፍቃድ መስጠት | 0..25 | ምትክ ንግድ ስራ ፍቃድ መስጠት በቁጥር | 70 | 80 | 90 | 125 |
| | | የንግድ ፍቃድ ስረዛዎች እንዲቀንሱ ማድረግ | 0.5 | የንግድ ስራ ፍቃድ ስረዛን በ60%መቀነስ | 60 | 90 | 100 | 350 |
| | | የንግድ ስያሜ መስጠት | 0..25 | የንግድ ስያሜ መስጠት በቁጥር | 68 | 92 | 100 | 2,600 |
| | | ነባር የንግድ ሥራ ፍቃድ ዕድሳት ማድረስ፤ | 0.8 | ነባር የንግድ ፍቃድ እድሳት በቁጥር | 2500 | 3000 | 3500 | 3600 |

| የተቋሙ ስትራቴጂያዊ ግብ5 | ክብደት | የግብ ተኮተግባራት | ክብደት | መለኪያ | ከ2013---- ታህሳስ 30 2015 አፈፃፀም መነሻ | ዓመታዊ ዒላማና አፈፃፀም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | የ2015(1/2) ዒላማ | የ2016 ዓመት ዒላማ | የ2017 ዓመት ዒላማ |
| | | የንግድ ስራ ፍቃድ ማሻሻያ | 0.5 | የንግድ ስራ ፍቃድ ማሻሻያ ማድረግ በቁጥር | 110 | 115 | 120 | 350 |
| | | የንግድ ምዝገባ ማሻሻያ | 0.5 | የተሠጠ የንግድ ምዝገባ ማሻሻያ በቁጥር | 70 | 80 | 90 | 350 |
| | | ቅርንጫፍ መስመዝገብ | 0.3 | የቅርንጫፍ መስመዝገብ በቁጥር | - | 85 | 100 | 150 |
| | | መረጃ መስጠት | 0..2 | የተሠጠ መረጃ በቁጥር | - | 15 | 20 | 30 |
| | | በንግድአዋጆች፣ፖሊሲዎች፣መመሪዎች፣ስትራቴጂዎች፣ህጎች፣ደንቦች ዙሪያ ለታችኛው የንግድ መዋቅርስልጠና መስጠት፣አቅም ማሳደግ | 0.15 | ግንዛቤ የተፈጠረላቸው የታችኛው ማዋቅር አካላት በቁጥር | - | 3 | 4 | 50 |
| | | ለባለድርሻ አካላት በንግድ አዋጆችና መመሪዎች ዙሪያ ግንዛቤ መስጠት፣ | 0.15 | ለባለድርሻ አካላት አዋጆችና መመሪዎች ዙሪያ ግንዛቤ መስጠት በቁጥር | - | 2000 | 2500 | 3500 |
| | | ከባለድርሻ አካላት፣ ከህዝብ ክንፍ እና ከተገልጋዮች ጋር የጋራ ምክክር መድረክ ማካሄድ፣ | 0.1 | የተደረገ የምክክር መድረክ በጊዜ | 1 | 3 | 4 | 12 |
| | | ጥራት ያለዉ ዕቅድ ማዘጋጀት፣ | 0.5 | ጥራት ያለዉ ዕቅድ ማዘጋጀት በሰነድ | 1 | 2 | 2 | 4 |
| ግብ፡-3<br>የበጀት አጠቃቀም | 1 | የሚመደበዉን በጀት ለታለመለት ዓላማ ማዋል | 1 | ለታለመለት ዓላማ የዋለ በጀት በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 |
| ግብ 4. የሰው ሀይል አቅም ማሳደግ | 1.2 | የዘርፉ እቅድ በተቀመጠው ዒላማዎች፣ ጥራትና ወቅት እንዲፈፀሙ ጠንካራ ክትትል፣ ድጋፍ ግምገማና ግብረ-መልስ ስርዓት መዘርጋት | 0.3 | ግምገማና ግብረ-መልስ ስርዓት መዘርጋት በጊዜ | 2 | 3 | 4 | 12 |

| የተቋሙ ስትራቴጂያዊ ግብ5 | ክብደት | የግብ ተኮተግባራት | ክብደት | መለኪያ | ከ2013----ታህሳስ 30 2015 አፈፃፀም መነሻ | ዓመታዊ ዒላማና አፈፃፀም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | የ2015(1/2) ዒላማ | የ2016 ዓመት ዒላማ | የ2017 ዓመት ዒላማ |
| | | የተገልጋዮችን የልማት ተነሳሽነት ለማጎልበት የሚያስችሉ የአሰራር ስርዓቶችን ለመቅሰም የአመለካከትና የክህሎት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና እና ልምድ ልዉዉጥ ማድረግ | 0.6 | የአመለካከትና የክህሎት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና እና ልምድ ልዉዉጥ ያገኙ አካላት በቁጥር | 1 | 10 | 10 | 20 |
| | | የመስክ ምልከታ ማድረግ እና ግብረ መልስ ስርዓት መዘርጋት | 0.3 | የተደረገ የመስክ ምልከታ በጊዜ | 6 | 15 | 12 | 24 |
| ግብ 5፡- ዘመናዊ የመረጃ አጠቃም ስርዓትን ማሳደግ | 1 | ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም የንግዱ ማህበረሰብ በኦን ላይን መረጃ ማስገበት | 1 | ወደ ቋት የገባ የነጋዴዎች መረጃ በቁጥር | 2045 | 3200 | 3500 | 4000 |
| ግብ፡- 6 ዘመናዊ የግብይት ስርዓት በመዘርጋት የበጀት አጠቃቀም ውጤታማ ማሳደግ | 1 | የግብይት አሰራርን በማዘመን በግብይት ዘርፍ የሚፈጠረዉን የካፒታል መጠን ማሳደግ | 0.25 | ከግብርና ምርቶች የተፈጠረ የካፒታል መጠን ብር(በሚሊዮን) | - | 2,500 | 30,000 | 50,000 |
| | | በግብርና ምርቶችና በግብይት ዘርፍ አቅም የሚያሳድግ የአጭር ጊዜ ስልጠና መስጠት | 0.25 | የተሰጠ ስልጠና በተሳታፊ ቁጥር | - | 4 | 12 | 15 |
| | | በቡና ምርት አቅራቢነት ለሚሰማሩ አዲስ የብቃት ማረጋገጫ መስጠጥ | 0.25 | ለቡና ምርት አቅራቢዎች አዲስ የብቃት ማረጋገጫ የተሠጣቸው በቁጥር | 1 | 6 | 12 | 24 |
| | | በቡና ጅምላና ቸርቻሪ ነጋዴ ለሚሰማሩ አዲስ የብቃት ማረጋገጫ መስጠት | 0.25 | ለቡና ጅምላና ቸርቻሪ አዲስ የብቃት ማረጋገጫ የተሠጣቸው አቅራቢዎች በቁጥር | 10 | 12 | 15 | 20 |

| የተቋሙ ስትራቴጂያዊ ግብ5 | ክብደት | የግብ ተኮተግባራት | ክብደት | መለኪያ | ከ2013---- ታህሳስ 30 2015 አፈፃፀም መነሻ | ዓመታዊ ዒላማና አፈፃፀም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | የ2015(1/2) ዒላማ | የ2016 ዓመት ዒላማ | የ2017 ዓመት ዒላማ |
| ግብ 7፡- በግብይት ዘርፍ አሰራር እና አደረጃጀት ማሻሻል | 2 | በቁም እንስሳት አድላቢነት ለሚሰማሩ አዲስ የብቃት ማረጋገጫ መስጠት | 0.29 | በቁም እንስሳት አድላቢነት አዲስ የብቃት ማረጋገጫ የተሠጣቸው ነጋዴዎች በቁጥር | 2 | 4 | 5 | 50 |
| | | በቆዳና ሌጦ አቅራቢነት ለሚሰማሩ አዲስ የብቃት ማረጋገጫ መስጠት | 0.29 | ለቆዳና ሌጦ ምርት አቅራቢዎች የተሠጠ አዲስ የብቃት ማረጋገጫ በቁጥር | 1 | 2 | 2 | 10 |
| | | በሉካንዳ ቤት ንግድ ለሚሰማሩ አዲስ የብቃት ማረጋገጫ መስጠት | 0.29 | በሉካንዳ ቤት ለሚሰማሩ ባለሀብቶች የተሠጠ አዲስ የብቃት ማረጋገጫ በቁጥር | 2 | 3 | 4 | 80 |
| | | ለቡና ጅምላና ችርቻሮ ነጋዴ ብቃት ማደስ፣ | 0.55 | የብቃት ማረጋገጫ የታደሰላቸው የየቡና ችርቻሮ አቅራቢዎች በቁጥር | 8 | 9 | 10 | 25 |
| | | ለቁም እንስሳት አድላቢነት ብቃት ማደስ፣ | 0.29 | የብቃት ማረጋገጫ የታደሰላቸው የየቁም እንስሳት አድላቢዎች በቁጥር | 1 | 2 | 2 | 30 |
| | | ለቆዳና ሌጦ አቅራቢዎች ብቃት ማደስ፣ | 0.29 | የብቃት ማረጋገጫ የታደሰላቸው የቆዳና ሌጦ አቅራቢዎች በቁጥር | 1 | 2 | 2 | 30 |
| | | ለሉካንዳ ቤቶች ብቃት ማደስ ፣ | 0.29 | የብቃት ማረጋገጫ የታደሰላቸው ሉካንዳ ቤቶች በቁጥር | 19 | 25 | 50 | 60 |
| ግብ 8፡- ዘመናዊ የግብይት | 9 | የከብት ቆዳን ለመጀመሪያ ደረጃ የገበያ ማዕከል ማቅረብ | 1 | የከብት ቆዳ በቁጥር | 5500 | 6000 | 7000 | 7100 |

| የተቋሙ ስትራቴጂያዊ ግብ5 | ክብደት | የግብ ተኮተግባራት | ክብደት | መለኪያ | ከ2013----ታህሳስ 30 2015 አፈፃፀም መነሻ | ዓመታዊ ዒላማና አፈፃፀም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | የ2015(1/2) ዒላማ | የ2016 ዓመት ዒላማ | የ2017 ዓመት ዒላማ |
| ስርዓትን በመዘርጋት የግብርና ምርት አቅርቦትን ማሳደግ | | የበግ ሌጦ ለመጀመሪያ ደረጃ የገበያ ማዕከል ማቅረብ | 0.5 | የበግ ሌጦ በቁጥር | 6,000 | 9,000 | 10,000 | 10,100 |
| | | የፍየል ሌጦ ለመጀመሪያ ደረጃ የገበያ ማዕከል ማቅረብ | 0.5 | የፍየል ሌጦ በቁጥር | 2100 | 2300 | 3000 | 4000 |
| | | የቁም እንስሳትን ለመጀመሪ ደረጃ የገበያ ማዕከል ማቅረብ | 1 | በቁጥር | - | 4000 | 4600 | 4,605 |
| | | የቡና ምርት ለሀገር ውስጥ ፍጆታ ማቅረብ | 0.4 | ለሀገር ውስጥ ፍጆታ የቀረበ ቡና በኩ/ል | 100 | 110 | 140 | 200 |
| | | የዳልጋ ከብት ለ1ኛ ደረጃ የገበያ ማዕከል ማቅረብ | 1 | የዳልጋ ከብት በቁጥር | 133595 | | | |
| | | በግና ፍየል ለ1ኛ ደረጃ የገበያ ማዕከል ማቅረብ | 1 | በግና ፍየል በቁጥር | 30000 | 32000 | 38,400 | 118,297 |
| | | የከብት ቆዳን ለመማዕከላዊ ገበያ ማቅረብ | 1 | የቀረበ የከብት ቆዳ በቁጥር | 34 | | | |
| | | የበግ ሌጦን ለማዕከላዊ ገበያ ማቅረብ | 0.5 | የቀረበ የበግ ሌጦ በቁጥር | | 3500 | 4,000 | 4,200 |
| | | የፍየል ሌጦን ለማዕከላዊ ገበያ ማቅረብ | 0.5 | የቀረበ የፍየል ሌጦ በቁጥር | | 2600 | 2800 | 3,000 |
| ግብ 9:- የግብይት መሰረተ ልማት ሽፋንን ማሳደግ | 2 | አዲስ የግብይት ማእከላትን በግብይት መስፈርት ማቋቋም | 1 | 1ኛ ደረጃ የቆዳና ሌጦ በቁጥር | - | | 1 | 2 |
| | | 1ኛ ደረጃ የሠሊጥና የጥራጥሬ የግብይት ማዕከላትን ማጠናከር | 0.43 | የሰሊጥ እና የጥራጥሬ 1ኛ ደረጃ በቁጥር | - | | | |
| | | 1ኛ ደረጃ የቁም እስሳት የግብይት ማዕከላትን ማጠናከር | 0.43 | የቁም እንስሳት 1ኛ ደረጃ በቁጥር | - | 2 | 2 | 10 |

| የተቋሙ ስትራቴጂያዊ ግብ5 | ክብደት | የግብ ተኮተግባራት | ክብደት | መለኪያ | ከ2013----ታህሳስ 30 2015 አፈፃፀም መነሻ | ዓመታዊ ዒላማና አፈፃፀም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | የ2015(1/2) ዒላማ | የ2016 ዓመት ዒላማ | የ2017 ዓመት ዒላማ |
| | | የግብይት መማዕከላት ፋሲሊቲ እንዲያሟሉ ማድረግ | 0.43 | 1ኛ ደረጃ የቁም ከብት ግብይት ማዕከል በቁጥር | 1 | 1 | 1 | 40 |
| | | | 0.43 | 2ኛ ደረጃ የቁም ከብት ግብይት ማዕከል በቁጥር | - | | 1 | 2 |
| ግብ 10፡- የገበያ ትስስርን በማጠናከር የተረጋጋ የገበያ ስርዓት አሠራርን ማሻሻል | 2 | በግብይት ዘርፍ ለሚሰማሩ ማህበራት(ዩነየኖች) የገበያ ትስስር መፍጠር | 1 | የገበያ ትስሰር ተጠቃሚ የሆኑ ማህበራት /ዩኒየኖች/ በቁጥር | - | 7 | 8 | 15 |
| | | በግብይት ዘርፍ ለሚሰማሩ አርሶ አደሮች የገበያ ትስስር መፍጠር | 0.5 | የገበያ ትስስር የተፈጠረላቸው አርሶ አደሮች በቁጥር | | 50 | 200 | 1000 |
| | | የግብይት ማዕከላቱ በአግባቡ አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን መከታተል | 0.25 | የተደረገ ክትትል ማዕከላት ቁጥር በድግግሞሽ | 31 | 36 | 40 | 95 |
| | | የግብይት ማዕከላት ግንባታዎችን መከታተል | 0.25 | የተደረገ ክትትል የተደረገባቸዉ ግንባታዎች በቁጥር | 3 | 6 | 8 | 10 |
| ግብ፡11 በኢንስፔክሽ ዘርፍ የሰው ሀይል አቅም ማሳደግ | 1.6 | በንግድ አዋጆች፣ ፖሊሲዎች፣መመሪዎች፣ስትራቴጂዎች፣ህጎች፣ደን ቦች ዙሪያ ለታችኛው የንግድ መዋቅር ስልጠና መስጠት፣ | 0.15 | የተሰጠ ስልጠና በተሳታፊ ብዛት | | | | |
| | | ለባለድርሻ አካላት በንግድ አዋጆችና መመሪዎች ዙሪያ ስልጠና መስጠት፣ | 0.15 | የተሰጠ ስልጠና በተሳታፊ ብዛት | | | 200 | 201 |
| | | ከባለድርሻ አካላት፣ከህዝብ ክንፍ እና ከተገልጋዬች ጋር የጋራ ምክክር መድረክ ማካሄድ፣ | 0.1 | የተሳተፉ ባለድርሻ አካላት በቁጥር | 109 | 180 | 200 | 230 |
| | | ለንግዱ ህብረተሰብ በጥራትና በደረጃዎች ዙሪያ ግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መስጠት፣ | 0.1 | የተሰጠ ስልጠና በተሳታፊ ብዛት | 46 | 60 | 200 | 210 |
| | | በየደረጃው ያሉ ግብርሀይሎችን አደረጃጀት ማጠናከርና ወደ ስራ እንዲገባ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣ | 1 | ክትትል የተደረገባቸው ግብረሀ-ይሎች በቁጥር | 3 | 20 | 22 | 24 |

| የተቋሙ ስትራቴጂያዊ ግብ5 | ክብደት | የግብ ተኮተግባራት | ክብደት | መለኪያ | ከ2013----ታህሳስ 30 2015 አፈፃፀም መነሻ | ዓመታዊ ዒላማና አፈፃፀም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | የ2015(1/2) ዒላማ | የ2016 ዓመት ዒላማ | የ2017 ዓመት ዒላማ |
| ግብ12፡-የገበያ ትስስርን በማጠናከር የተረጋጋ የገበያ ስርዓት አሠራርን ማሻሻል | 1 | የዘርፉ እቅድ በተቀመጠው ዒላማዎች፣ ጥራትና ወቅት እንዲፈፀሙ ጠንካራ ክትትል፣ ድጋፍ ግምገማና ግብረ-መልስ ስርዓት መዘርጋት | 0.5 | የተደረገ ክትትልና ድጋፍ በጊዜ | 1 | 2 | 3 | 24 |
| | | | 0.6 | የተሰጠ ግብረ-መልስ በሰነድ | 2 | 3 | 4 | 4 |
| | | በግብይት ዘርፍ ለሚሰማሩ አርሶ አደሮች የገበያ ትስስር መፍጠር | 0.25 | የገበያ ትስስር የተፈጠረላቸው አርሶ አደሮች በቁጥር | | | 400 | 3000 |
| | | የገበያ ትስስርን በመፍጠር በንግዱ ዘርፍ የሚታየውን የዋጋ ንረት ማረጋጋት | 0.5 | የገበየያ ትስሰስር የተፈጠረላቸው አምራቾች/ነጋዴዎች/ በቁጥር | 5 | 15 | 20 | 25 |
| | | | 0.25 | የገበየያ ትስሰስር የተፈጠረላቸው ዩኒየኖች በቁጥር | 8 | 25 | 40 | 45 |
| ግብ፡-13 ፡የኢንስፔክሽእና ሬጉላቶሪ ስራዎችን ማሻሻል | 2.5 | በህገ-ወጥ ንግድ መንስኤ ላይ ጥናት ማካሄድ | 0.4 | የተደረገ ጥናት በሰነድ | 1 | 2 | 2 | 4 |
| | | | 0.4 | ካበሬት የተደረገ የስነ ልክ መሳሪያዎች በቁጥር | 450 | 780 | 1000 | 1100 |
| | | ከአጎራባች ወረዳዎች ጋር በመደጋገፍ ህገ ወጥ ንግድን መከላከል | 0.4 | የተካሄደ መድረክ በቁጥር | 2 | 3 | 4 | 8 |
| | | የንግድ ምዝገባና የንግድ ስራ ፈቃድ እድሳትና አሰጣጥ ኢንስፔክሽን ማካሔድ | 0.4 | የንግድ ምዝገባ በቁጥር | 250 | 260 | 2000 | 2008 |
| | | | 0.4 | የንግድ ፍቃድ በቁጥር | 250 | 260 | 2,000 | 2,008 |

| የተቋሙ ስትራቴጂያዊ ግብ5 | ክብደት | የግብ ተኮተግባራት | ክብደት | መለኪያ | ከ2013----ታህሳስ 30 2015 አፈፃፀም መነሻ | ዓመታዊ ዒላማና አፈፃፀም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | የ2015(1/2) ዒላማ | የ2016 ዓመት ዒላማ | የ2017 ዓመት ዒላማ |
| ግብ፡-14 የመለኪያ መሳሪያዎችን ትክክለኛነት ከማረጋገጥ | 6 | የዳቦ ሚዛን ቬሪፋይ ማድረግ | 0.43 | የዳቦ ልኬት ማስኬድ በቁጥር | 9 | 20 | 30 | 45 |
| | | የጠረጴዛ ሚዛን ቬሪፋይ ማድረግ | 0.43 | የጠረንጴዛ ሚዛን በቁጥር | 278 | 280 | 360 | 300 |
| | | የምድር ሚዛን ቬሪፋይ ማድረግ | 0.43 | የምድር ሚዛን በቁጥር | 180 | 190 | 250 | 290 |
| | | አናሎግ የስጋ ሚዛኖችን ቬሪፋይ ማድረግ | 0.43 | አናሎግ /የስጋ ሚዛን በቁጥር | 48 | 50 | 52 | 60 |
| | | ዲጂታል የወርቅ ሚዛኖችን ቬሪፋይ ማድረግ | 0.43 | ድጅታል/የወርቅ ሚዛን በቁጥር | - | 20 | 24 | 25 |
| | | በመለኪያ መሳሪያዎች ላይ ፊዚካል እንስፔክሽን ማካሄድ | 0.42 | የተደረገ ፊዚካል ኢንስፔክሽን በቁጥር | 20 | 22 | 24 | 50 |
| | | በንግድ ድርጅቶች ላይ ኢንስፔክሽን በማድረግ አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃ መዉሰድ | 1.5 | ኢንስፔክሽን የተደረገላቸዉ በተቋማት ቁጥር | 18 | 20 | 24 | 28 |
| | | በፋብሪካ ላይ የኢንስፔክሽን ስራዎች መስራት | 0.5 | በፋብሪካ ቁጥር | 1 | 8 | 13 | 20 |
| | | የአስገዳጅ የሰብል ምርቶችን እንስፔክሽን ማድረግ | 0.5 | ክትትል የተደረገባቸው ድርጅቶች በጊዜ | - | 12 | 12 | 24 |
| | | የመሰታዊ ሸቀጦች የገበያ ፍላጎት፣ አቅርቦትና ገበያ ጉድለት በመለየት አቅርቦትን ማሟላት | 0.7 | መሠረታዊ ምርቶችን ያቀረቡ ማህራት/ዩኒየኖች/ | 2 | 3 | 4 | 35 |
| ግብ፡-15 የሸማቹን መብትእና ደህንነት ማረጋገጥ | 7 | የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ጽንሰ ሃሳብና የህግ ይዘቶችን ለነጋዴው ማህበረሰብ ማህበረሰብ ትምህርት መስጠት | ~ | የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ጽንሰ ሃሳብና የህግ ይዘቶችን ለነጋዴው ማህበረሰብ ትምህርት መስጠት በቁጥር | 1200 | 1300 | 1,500 | 1,550 |

| የተቋሙ ስትራቴጂያዊ ግብ5 | ክብደት | የግብ ተኮተግባራት | ክብደት | መለኪያ | ከ2013----ታህሳስ 30 2015 አፈፃፀም መነሻ | ዓመታዊ ዒላማና አፈፃፀም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | የ2015(1/2) ዒላማ | የ2016 ዓመት ዒላማ | የ2017 ዓመት ዒላማ |
| | | በት/ት ተቋማት የሸማች ክበብ ማቋቋም እና ማጠናከርን ከ4 ወደ 6 ማሳደግ | 1.5 | በት/ቤቶች የሸማች ክበብ ማቋቋም በቁጥር | 4 | 5 | 6 | 10 |
| | | ሸማቹን የሚያሳስቱ የህትመትና የኢሌክትሮኒክስ ማስታወቂያዎች በየወሩ መረጃ በመሰብሰብ እንዲታገዱ ወይም ማስተካከያ እንዲደረግባቸው ማድረግ | 1.5 | ሸማቹን የሚያሳስቱ የህትመትና የኢሌክትሮኒክስ ማስታወቂያዎች በየወሩ መረጃ በመሰብሰብ በቁጥር | - | 15 | 24 | 30 |
| | | የማህበረሰቡን/የሸማቹን ጤና ለማስጠበቅ የምርትና አገልግሎቶችን ጥራትና ደህንነት በየሳምንቱ መከታተል | 1.5 | የማህበረሰቡን/የሸማቹን ጤና ማስጠበቅ በግዜ | 17 | 20 | 24 | 48 |
| | | በእርቅና ድርድር እንዲታዩ ከሚቀርቡ ጉዳዮች መካከል 75% በማስማማት የሸማቹ መብትና ጥቅም እንዲጠበቅ ማድረግ፤ | 1..5 | በእርቅና ድርድር እንዲታዩ ማድረግ | 60 | 67 | 75 | 100 |
| ግብ፡-16 | 3 | በመሰረታዊ ፍጆታ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ለሸማች ማህበረት የሚቀረበውን የስኳር ስርጭት ማድረግ ፤ | | ስኳር ስርጭት ማድረግ በኩንታል | 980 | 1000 | 1500 | 1600 |
| | | | 1 | የምግብ ዘይት ስርጭት ማድረግ በሊትር | 144,000 | 154,000 | 155,000 | 155,010 |
| | | በወረዳችን 5ቱም ቀበሌዎች የመህበራዊ ችግር ላካጠማችዉ የመ/ሰብ ክፍሎች ዘይት ና ሱኳር | 0.5 | ሱኳር በኩንታል | | 52 | 52 | 60 |
| | | | 0.5 | ዘይት በሊትር | 400 | 450 | 500 | 550 |
| | | የመሰታዊ ሸቀጦች የገበያ ፍላጎት፣ አቅርቦትና ገበያ ጉድለት በመለየት አቅርቦትን ማሟላት | 1 | አቅርቦትና ገበያ ጉድለት በመለየት አቅርቦትን ማሟላት በጥናት ሰነድ | | 3 | 4 | 4 |

| የተቋሙ ስትራቴጂያዊ ግብ5 | ክብደት | የግብ ተኮተግባራት | ክብደት | መለኪያ | ከ2013----ታህሳስ 30 2015 አፈፃፀም መነሻ | ዓመታዊ ዒላማና አፈፃፀም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | የ2015(1/2) ዒላማ | የ2016 ዓመት ዒላማ | የ2017 ዓመት ዒላማ |
| ግብ፡- 17 የኢንዱስትሪልማት ማሳደግ | 5 | የኢንዱስትሪ ልማትን ለማሳደግ የተከለሉ የኢንዱስትሪ ፓርክ ማሳድግ | 2 | የኢንዱስትሪ ፓርክ ማሳደግ በሄክታር | | | | |
| | | የኢንዱስትሪ ክላስተር እንዲከላል ማድረግ | 1 | የኢንዱስትሪ ክላስተር እንዲከላል ማድረግ በሄክታር | 361 | 362 | 365 | 367 |
| | | ከሚከለለው የኢንዱስትሪ ክላስተር ውስጥ 75 ሄክታር ማልማት | 1.5 | የኢንዱስትሪ ክላስተር ማልማት በመቶኛ | | | 50 | 80 |
| | | የኢንዱስትሪ ክላስተር ለአነስተኛ እና መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች 2 የማምረቻ ሼድሰርቶ ማስተላለፍ | 0.5 | አምራች ኢንዱስትሪዎች 2 የማምረቻ ሼድ ሰርቶ ማስተላለፍ በቁጥር | | | 2 | 3 |
| ግብ፡-18፡- አዲስ አነስተኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎችን ማቋቋም | 3 | ለኢንዱስትሪ ፓርክ አጠቃላይ ስራን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤ | 0.5 | ለኢንዱስትሪ ፓርክ አጠቃላይ ስራን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤ | | 12 | 16 | 17 |
| | | ብረታ-ብረት ንዑስ ዘርፍ በቁጥር | 0.65 | ብረታ-ብረት ዘርፍ በቁጥር | 4 | 35 | 45 | 50 |
| | | እንጨት ንዑስ ዘርፍ በቁጥር | 0.65 | እንጨት ዘርፍ በቁጥር | 1 | 30 | 45 | 47 |
| | | ኮንስትራክሽን ግብዓት ንዑስ ዘርፍ በቁጥር | 0.65 | ኮንስትራክሽን ግብዓት ዘርፍ በቁጥር | | 32 | 38 | 45 |
| | | አግሮ ፕሮሰሲንግ ንዑስ ዘርፍ በቁጥር | 0.64 | አግሮ ፕሮሰሲንግ ንዑስ ዘርፍ በቁጥር | 1 | 2 | 5 | 8 |

| የተቋሙ ስትራቴጂያዊ ግብ5 | ክብደት | የግብ ተኮተግባራት | ክብደት | መለኪያ | ከ2013----ታህሳስ 30 2015 አፈፃፀም መነሻ | ዓመታዊ ዒላማና አፈፃፀም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | የ2015(1/2) ዒላማ | የ2016 ዓመት ዒላማ | የ2017 ዓመት ዒላማ |
| ግብ፡-19 የአምራች ኢንዱስትሪዎች የማምረት አቅም ማሳደግ | 1 | የአምራች ኢንዱስትሪዎች የማምረት አቅም በመቶኛ | 1 | ኢንዱስትሪዎች የማምረትአቅማቸውን ከ15% ወደ 35% ማሳደግ | 2% | 15% | 20% | 30% |
| ግብ፡-20 መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ | 1 | ዘመናዊ የሂሳብ አሰራር ተጠቃሚ የሆኑ አነስተኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች በቁጥር | 0.2 | ዘመናዊ የሂሳብ አያያዝ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ በቁጥር | 2 | 8 | 15 | 20 |
| | | ዘመናዊ የሂሳብ አሰራር ተጠቃሚ የሆኑ መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች በቁጥር | 0.2 | ዘመናዊ የሂሳብ አያያዝ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ በቁጥር | | | 8 | 15 |
| | | ዘመናዊ የሂሳብ አሰራር ተጠቃሚ የሆኑ መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች በቁጥር | 0.2 | ዘመናዊ የሂሳብ አያያዝ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ በቁጥር | 1 | 8 | 10 | 15 |
| ግብ፡-21 አነስተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች የደረጃ ሽግግር እንዲያደርጉ ማድረግ፣ | 0.2 | የአምራች ኢንዱስትሪዎች የማምረቻ ቦታ ችግር እንዲፈታ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራት፣ | 0.2 | የአምራች ኢንዱስትሪዎች የማምረቻ ቦታ ችግር መፍታት በቁጥር | 1 | 8 | 10 | 15 |
| | | ዘርፉን ከማንቃት አንፃር የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄን ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ተግባራዊ ማድረግ | 0.1 | የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄን ማሳደግ በግዜ | | | 4 | 6 |

| የተቋሙ ስትራቴጂያዊ ግብ5 | ክብደት | የግብ ተኮተግባራት | ክብደት | መለኪያ | ከ2013---- ታህሳስ 30 2015 አፈፃፀም መነሻ | ዓመታዊ ዒላማና አፈፃፀም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | የ2015(1/2) ዒላማ | የ2016 ዓመት ዒላማ | የ2017 ዓመት ዒላማ |
| | | በተለያዩ ምክንያቶች ማምረት የቆሙኢንዱስትሪዎችን እንዲጠናከሩ ድጋፍ ማድረግ | 0.1 | ኢንዱስትሪዎችን እንዲጠናከሩ ድጋፍ ማድረግ በግዜ | 2 | 3 | 5 | 8 |
| ግብ:22 ለአምራች ኢንዱስትሪዎች የሚፈጠረውን የግብዓትና | 2 | ለአነስተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች የግብዓት አቅርቦት ትስስር እንዲፈጥሩ ድጋፍ ማድረግ | 0.74 | አምራች ኢንዱስትሪዎች ትስስር እንዲፈጥሩ ድጋፍ ማድረግ በቁጥር | 3 | 4 | 5 | 80 |
| | | ለመካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች የግብዓት አቅርቦት ትስስር እንዲፈጥሩ ድጋፍ ማድረግ | 0.74 | ለመካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች ትስስር እንዲፈጥሩ ድጋፍ ማድረግ | 0 | | 3 | 4 |
| | | አምራች ኢንዱስትሪዎች የግብዓት አቅርቦት እንዲያገኙ ከባለድርሻ አካላት ጋር መስራት | 0.74 | አምራች ኢንዱስትሪዎች ከባለድርሻ አካላት ጋር መስራት | 0 | | 10 | 20 |
| ግብ፡- 23 የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የእድገት ምጣኔን ማሳደግ (3.5) | 3.3 | አነስተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎችን አዲስ በማቋቋም የስራ እድል በመፍጠር ከዚህም ወስጥ ሴቶች 30 በመቶ እና ወጣቶች 74 እንዲያደግ ማድረግ | 0.5 | አነስተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎችን አዲስ በማቋቋም የስራ እድል መፍጠር | 5 | 65 | 80 | 90 |
| | | በብረታብረት እና በእንጨት ስራ የተፈጠረ የስራ እድል | 2 | በብረታብረት እና በእንጨት ስራ የስራ እድል መፍጠር | 60 | 67 | 85 | 100 |
| | | በጨርቃ ጨርቅ እና በአልባሳት ስራ የተፈጠረ የስራ እድል በቁጥር | 1 | በጨርቃ ጨርቅ እና በአልባሳት የስራ እድል መፍጠር | 12 | 17 | 20 | 140 |
| 24.የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የእድገት ምጣኔን ማሳደግ(3) | 3 | በአግሮ ፕሮሰሲንግ ዉጤቶች የተፈጠረ የስራ እድል በቁጥር | 1 | በአግሮ ፕሮሰሲንግ ዉጤቶች የስራ እድል መፍጠር በቁጥር | | 32 | 50 | 55 |
| | | በኮንስትራክሽ ግብአት፤ጌጣጌጥ፤ኬሚካልና ማእድን የተፈጠረ የስራ እድል | 0.3 | በኮንስትራክሽ ግብአት፤ጌጣጌጥ፤ኬሚካልና ማእድን የስራ እድል መፍጠር በቁጥር | 40 | 42 | 50 | 51 |
| | | አነስተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎችን አዲስ በማቋቋም የስራ እድል በመፍጠር ከዚህም ወስጥ የሴቶችን ተሳትፎ ማሳደግ | 0.3 | አነስተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎችን አዲስ በማቋቋም የሴቶችን ተሳትፎ ማሳደግ በቁጥር | 20 | 27 | 30 | 61 |
| | | መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎችን አዲስ በማቋቋም የስራ እድል በመፍጠር ሴት | 0.3 | በአግሮ ፕሮሰሲንግ ዉጤቶች የተፈጠረ የስራ እድል በቁጥር | | 30 | 60 | 55 |

| የተቋሙ ስትራቴጂያዊ ግብ5 | ክብደት | የግብ ተኮተግባራት | ክብደት | መለኪያ | ከ2013---- ታህሳስ 30 2015 አፈፃፀም መነሻ | ዓመታዊ ዒላማና አፈፃፀም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | የ2015(1/2) ዒላማ | የ2016 ዓመት ዒላማ | የ2017 ዓመት ዒላማ |
| | | ወጣቶችን ተሳትፎ ማሳደግ | 0.3 | በብረታብረት እና በእንጨት የስራ እድል መፍጠር በቁጥር | | 55 | 60 | 100 |
| | | | 0.3 | በጨርቃ ጨርቅ እና በአልባሳት የስራ እድል መፍጠር በቁጥር | 16 | 18 | 20 | 50 |
| | | | 0.2 | በኮንስትራክሽግብአት፤ጌጣጌጥ፤ኬሚካልማእድን የስራ እድል መፍጠር በቁጥር | 1 | 1 | 1 | 5 |
| ግብ፡-25 የአምራች ኢንተርፕራይዞችን የተኪ ምርት | 0›6 | በአግሮ ፕሮሰሲንግ የተተኩ ምርቶች መጠን ማሳደግ | 0.3 | በአግሮ ፕሮሰሲንግ የተተኩ ምርቶች መጠን 30% ማሳደግ | | | | |
| | | የኮንስትራክሽን ግብዓት፣ ኬሚካል፣ ጌጣጌጥና አምራች የተተኩ ምርቶች መጠን ማሳደግ | 0.3 | የኮንስትራክሽን ግብዓት፣ ኬሚካል፣ ጌጣጌጥና አምራች የተተኩ ምርቶች መጠን ማሳደግ በቁጥር | 65 | 67 | 68 | 70 |
| | | ተኪ ምርቶችን በማምረት ይወጣ የ ነበረውን የውጭ ምዛሬ ማስቀ | 0.08 | ተኪ ምርቶችን በማምረት ይወጣ የነበረውን 30% የውጭ ምንዛሬ ማስቀረት | | | 1% | 2% |
| ግብ፡-26 የመንገድ | 10 | በገጠር መደበኛ የህዝብ የትራንስፖርት የሚሰጥባቸው መስመሮች በቁጥር | 1 | በቁጥር | | | | |
| | | በከተማ መደበኛ የህዝብ የትራንስፖርት የሚሰጥባቸው መስመሮች በቁጥር | 1 | በቁጥር | | 265 | 281 | 300 |
| | | ለአነስተኛና መለስተኛ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች የተሰጠ ስምሪት ምልልስ በቁጥር | 1 | በቁጥር | 4200 | 4500 | 50,000 | 50,500 |
| | | የትራንስፖርት አገልግሎት በመናኻሪያ ስምሪት በምልልስ የተጓጓዘ ህዝብ በቁጠር | 2 | በቁጥር | | | | |
| | | ከትራነሰፖርት አገልግሎት የተሰበሰበ ገቢ | 4 | በብር | 4000 | 500,50 | 600,000 | 600,400 |
| | | በህዝብ ማመላለሺያ ተሽከርካሪዎች ላይ ክትትልና ቁጥጥር ስራ ማከናወን | 1 | በየቀኑ | 1 | 2 | 3 | 4 |

| የተቋሙ ስትራቴጂያዊ ግብ5 | ክብደት | የግብ ተኮተግባራት | ክብደት | መለኪያ | ከ2013---- ታህሳስ 30 2015 አፈፃፀም መነሻ | ዓመታዊ ዒላማና አፈፃፀም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | የ2015(1/2) ዒላማ | የ2016 ዓመት ዒላማ | የ2017 ዓመት ዒላማ |
| ግብ፡-27 የከተማ ነዋሪ በታክሲ ትራንስፖርት ተጠቃሚ ማድረግ | 2 | በከተማ ታክሲ በምልልስ የተጓጓዘ ህዝብ በቁጠር | 2 | በጊዜ | 28000 | 49,000 | 50,000 | 50,100 |
| ግብ፡- 28 የህዝብ ትራንስፖርት ማህበራት በተደራጁ ልክ አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ | 5 | በመናኻሪያ ውስጥ ያሉት 6ቱ የህዝብ ትራንስፖርት የማህበራት ለተሸከርካሪዎቻቸው በተቀመጠው ደረጃ መሰረት ስምሪት በየጊዜው መከታተል | 2.5 | በየወሩ | | | | |
| | | 3ቱ የከተማ ታክሲ ማህበራት በስራቸው ለታቀፉት ተሽከርካሪዎች ስምሪት በአግባቡ እየተሰጠ መሆኑን በየጊዜው መከታተል፣ | 2.5 | በየወሩ | 10 | 11 | 12 | 35 |
| ግብ፡-29 ትምህርትና ግንዛቤ ማሳደግ | 5 | በመንገድ ትራፊክ ደህንነት ዙሪያ ለህብዝቡ ግንዛቤ መፍጠር | 0.8 | በቁጥር | 38,000 | 40,000 | 40,220 | 42,500 |
| | | የህዝብንቅናቄ በመፍጠር ለህብረተሰቡ የመንገድ አጠቃቀም ግንዛቤ ማድረግ | 0.8 | በቁጥር | 38,000 | 40,000 | 40,220 | 42,500 |
| | | በት/ቤቶችና በመነህሪያ ውስጥ በሚኒሚዲያ ስለመንገድ ደህንነት ግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ለህብረተሰቡ መስጠት | 0.8 | በቁጥር | 10 | 11 | 12 | 13 |
| | | በማስ ሚዲያ የህብረተሰቡን የመንገድ ደህንነትግንዛቤ ማሳደግ | 0.8 | በቁጥር | 10 | 11 | 12 | 13 |

| የተቋሙ ስትራቴጂያዊ ግብ5 | ክብደት | የግብ ተኮተግባራት | ክብደት | መለኪያ | ከ2013----ታህሳስ 30 2015 አፈፃፀም መነሻ | ዓመታዊ ዒላማና አፈፃፀም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | የ2015(1/2) ዒላማ | የ2016 ዓመት ዒላማ | የ2017 ዓመት ዒላማ |
| | | በት/ቤቶች የተቋቋሙ የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ክበባት ቁጥር ማሳደግ | 0.9 | በቁጥር | 5 | 7 | 8 | 20 |
| | | በቀበሌዎች የመንገድ ትራፊክ ም/ቤቶች ማቋቋምና ማጠናከር | 0.9 | በቁጥር | 2 | 4 | 5 | 16 |
| ግብ፡-30 የቁጥጥር እና እርምት | 9 | በተሽከርካሪዎች ላይ ድንገተኛ የቴክኒክ ምርመራ ማድረግ | 1.5 | በቁጥር | 1,200 | 13,300 | 13,400 | 13,500 |
| | | የትራፊክ ቁጥጥርና ደንብ ማስከበር ስራ ማከናወን/በምልልስ/ | 1.7 | በቁጥር | 250 | 300 | 360 | 362 |
| | | ከትራፊክ ደንብ መተላለፍ ከቅጣት የሚገኝ ገቢ | 2.6 | በብር | | 620,000 | 650,000 | 680,000 |
| | | በትራንስፖርት ደምብ ጥሰት በሪከርድ የተመዘገቡ አሽከርካሪዎች | 1 | በቁጥር | 4000 | 4500 | 5000 | 5100 |
| | | የደህንነት ቀበቶ አጠቃቀምን ካሉት 2162 ተሽከርካሪዎች 30 ፐርሰንት ተግባራዊ ማድረግ | 0.7 | በቁጥር | 1875 | 1,900 | 5000 | 6000 |
| | | በከተሞች የከተማ ትራንስፖርት አገልግሎት መስጫ ተርሚናሎች /ፈርማታዎች እንዲሰሩ ይደረጋል | 1 | በቁጥር | 1 | 2 | 2 | 6 |
| | | በፌድራል የወጣው የትራንስፖርት መቆጣጠሪያ ደንብ ቁጥር 395/2009 እና በክልሉ በወጣው ተሸሽሎ የወጣውን መመሪያ ቁጥር 20 | 0.5 | በጊዜ | 12 | 90 | 100 | 125 |